የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፳፩
አዲስ አበባ–ታህሣሥ ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፭

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

9th Year No. 21
ADDIS ABABA–31st December, 2002

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፫፻፰/፲፱፻፺፭ ዓ.ም
የተርን ኦቨር ታክስ
አዋጅ ...................................................... ገጽ ፪ሺ፳፬

## አዋጅ ቁጥር ፫፻፰/፲፱፻፺፭
## የተርን ኦቨር ታክስ ለማስከፈል
## የወጣ አዋጅ

ቁጠባንና ኢንቬስትመንት ለማሳደግ ፣ ታክስ ከመክፈል ለመሸሽ ወይም በሕጉ ውስጥ የሚታየውን ክፍተት በመጠቀም ታክሱን ላለመክፈል የሚደረገው ጥረት ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት ለመቀነስ፣ የኢኮኖሚ ዕድገትን ለማፋጠን፣ እና በጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርትና በመንግሥት ገቢ መካከል ያለውን ግንኙነት ለማሻሻል፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ በሥራ ላይ እንዲውል የተወሰነ በመሆኑ ፣

የተጨማሪ እሴት ታክስን አስተዳደር አመቺነት ግምት ውስጥ በማስገባት ለታክሱ የሚመዘገቡ ሰዎች ታክስ የሚከፈልበት ዓመታዊ ግብይት ከብር ፭፻ሺ በላይ እንዲሆን የተወሰነ ስለሆነ፣

በንግድ ግንኙነት ውስጥ ፍትሐዊነትን ለማስፈን ፣ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተመዘገቡ ሰዎች ግዴታቸውን እንዲወጡ፣ እና የታክስ ሥርዓቱን ሽፋን የተሟላ ለማድረግ የማስተካከያ ተርንኦቨር ታክስ አዋጅ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

፩· **አጭር ርዕስ**
ይህ አዋጅ "የተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር ፫፻፰/፲፱፻፺፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## CONTENTS

Proclamation No. 308/2002
Turnover Tax
Proclamation ............................................ Page 2024

## PROCLAMATION NO. 308/2002
## TURNOVER TAX PROCLAMATION

*WHEREAS,* it has been determined that there shall be enacted a value-added tax to enhance saving and investment, minimize the damage that may be caused by attempts to avoid or evade taxes, stimulate economic growth, and improve the relationship between Gross Domestic Product and Government Revenue;

*WHEREAS,* administrative feasibility considerations limit the registration of persons under the value-added tax to those with annual taxable transactions the total value of which exeeds 500,000 Birr;

*WHEREAS,* an equalization turnover tax imposed on persons not registered for value-added tax allows them to fulfill their obligations and also enhances fairness in commercial relations and makes complete the coverage of the tax system;

*NOW, THEREFORE,* in accordance with Article 55(1) and (11) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

### SECTION ONE
### General

1. *Short Title*
This Proclamation may be cited as the "Turnover Tax Proclamation No.308/2002."

ያንዱ ዋጋ 4.85
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪· ትርጓሜ

፩· በዚህ አዋጅ ውስጥ ትርጉም ያልተሰጣቸው ቃላትና ሐረጐች በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፭/፲፱፻፺፬ (ከዚህ በኋላ "የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ" ተብሎ በሚጠቀሰው) ውስጥ የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ፤

፪· "ጠቅላላ የሽያጭ ገቢ" ማለት የወጪ ተቀናሽ ሳይደረግ የተገኘ ጠቅላላ ገቢ ሲሆን ፣ የተሸጡት ዕቃዎች የተመረቱበትን ወይም የተገዙበትን ዋጋ ይጨምራል፤

፫· "ታክስ የሚከፈልበት ግብይት" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯ ከተርን ኦቨር ታክስ ነፃ ከተደረገው ግብይት በስተቀር በንግድ ሥራ ሂደት ወይም የንግድ ሥራን እንቅስቃሴ ለማሻሻል በሚደረግ ጥረት ዕቃዎችን ማቅረብ ወይም አገልግሎቶችን መስጠት ነው ፤

፬· "ለተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተመዘገበ ሰው" ማለት በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፭/፲፱፻፺፬ አንቀጽ ፲፮ እና ፲፯ በተደነገገው መሠረት ዓመታዊ የሽያጭ እንቅስቃሴው ከብር ፭፻ሺ ወይም ሚኒስትሩ ከሚወስነው መጠን በታች በመሆኑ ምክንያት ወይም በፈቃደኝነት ያልተመዘገበ ሰው ነው፤

፭· "ሰው" ማለት ማንኛውም ግለሰብ ፣ ድርጅት ወይም ማኅበር ሲሆን ፣ ሌላን ሰው በመወከል ተቀማጭነቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ሆኖ የንግድ ሥራ የሚያካሂድን የንግድ ወኪል ይጨምራል፤

፮· "ድርጅት" ማለት የንግድ ሥራ የሚያካሂድ ማናቸውም ኩባንያ ወይም የተመዘገበ የሽርክና ማኅበር ወይም ከተመዘገበ የሽርክና ማኅበር ጋር ተመሳሳይ የሆነና በውጭ አገር ሕግ መሠረት የተቋቋመ ድርጅት ወይም ማናቸውም የመንግሥት የልማት ድርጅት ወይም የገንዘብ ድርጅት ሲሆን ፣ በውጭ አገር ያለን አካል በመወከል በኢትዮጵያ ውስጥ የንግድ ሥራ የሚያካሂደውን ወኪል እና ፀንቶ በሚሠራበት በኢትዮጵያ ወይም በሌላ አገር ሕግ የተመሠረተ ወይም ዕውቅና ያገኘ ቢሆንም ባይሆንም እንደ ድርጅት የሚንቀሳቀስን ይጨምራል ፤

፯· "ዕቃ" ማለት የልውውጥ ዋጋ ያለው ፣ ጠቀሜታ የሚሰጥ ወይም ፍላጐት የሚያሟላ ማናቸውም ዕቃ ወይም ሸቀጥ ሲሆን እንስሳትንም ይጨምራል፤

፰· "ሽያጭ" ማለት ዕቃዎችን በጥሬ ገንዘብ ወይም በዓይነት መገበያየት እና የተወሰነ ክፍያ በመቀበል አገልግሎት መስጠት ሲሆን ፣ ታክስ ከፋዩ ያለክፍያ የሚሰጣቸውን ዕቃዎች ወይም የሚያቀርባቸውን አገልግሎቶች ይጨምራል፤

፱· "አገልግሎት" ማለት የዕቃዎችን ዝውውር የማይጨምር በክፍያ የሚከናወን ማናቸውም ተግባር ነው፤

፲· "የታክስ ባለሥልጣን" ማለት የፌዴራል አገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ዋና መሥሪያ ቤት እና በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የተቋቋሙ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶቹ እንዲሁም የየክልሉ እና የከተማ መስተዳድሮች የገቢ ሰብሳቢ አካላት ናቸው፤

፲፩· "ታክስ" ማለት የዕቃዎች ወይም የአገልግሎቶች ሽያጭ በተከናወነ ቁጥር የሚከፈል ተርን ኦቨር ታክስ ነው፤

፲፪· "ታክስ ከፋይ" ማለት የተርን ኦቨር ታክስ ሰብስቦ ለታክሱ ባለሥልጣን ገቢ እንዲያደርግ ግዴታ የተጣለበት ሰው ነው፤

፲፫· "ሚኒስቴር" እና "ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እና ሚኒስትር ነው።

2. *Definitions*

1) For the purpose of this Proclamtion, unless defined otherwise in this Proclamation, terms used herein shall have the meaning as defined in the Value-Added Tax Proclamation No. 285/2002 (hereinafter referred to as the ''VAT Proclamation'');

2) ''Gross Receipts'' means income, without reduction of expenses, including the cost of goods sold;

3) ''Taxable Transaction'' means a supply of goods or a rendition of services in the course or furtherance of a taxable activity, other than an exempt transaction described in Article 7 of this Proclamtion;

4) ''Person not Registered for VAT'' means a person who, according to Article 16 and 17 of the Value Added Tax Proclamation, is not registered by reason of his annual turnover being below Birr 500,000 or threshold set by the Minister; or by reason of not having applied for voluntary registration;

5) ''Person'' shall mean any individual, body or association of persons and includes a business representative residing and doing business in Ethiopia on behalf of the principal;

6) ''Body'' shall mean any company, registered partnership, entity formed under foreign law resembling a company or resgistered partnership; or any public enterprise or financial agency that carries out business activities including body of persons corporate or unincorporated whether created or recognized under a law in force in Ethiopia or elsewhere, and any foreign body's business agent doing business in Ethiopia on behalf of the principal;

7) ''Goods'' means any type of goods or commodity that has exchange value, utility and brings about satisfaction, and includes animals;

8) ''Sale'' means exchange of goods in cash or in kind and rendering of services upon receipt of payment, and includes goods supplied or services rendered by the taxpayer free of charge;

9) ''Service'' means work done for others which does not result in the transfer of goods;

10) ''Tax Authority''means the Federal Inland Revenue Authority and the tax authorities of the Regional States and city administrations;

11) ''Tax'' means Turnover Tax payable whenever transaction of sales of goods and services is carried out;

12) ''Taxpayer''means a person obliged to collect and transfer Turnover Tax to the Tax Authority;

13) ''Ministry'' and ''Minister'' means the Ministry and Minister of Finance and Economic Development, respectively.

፫· **የአዋጁ ተፈጻሚነት**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፯ ወይም አዋጁን መሠረት በማድረግ በሚወጣው መመሪያ ነፃ ካልተደረጉ በስተቀር፣ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተመዘገቡ ሰዎች በአገር ውስጥ በሚሸጡ ዋቸው ዕቃዎች እና አገልግሎቶች ላይ በዚህ አዋጅ መሠረት ተርን ኦቨር ታክስ ይከፈላል።

**ክፍል ሁለት**

**የታክስ ማስከፈያ ልክ ስለመወሰን እና ከታክሱ ነጻ ስለማድረግ**

፬· **የተርን ኦቨር ታክስ ተመን**

፩· በማናቸውም በአገር ውስጥ በሚሸጡ ዕቃዎች ላይ ፪ በመቶ (ሁለት ፐርሰንት)

፪· በአገር ውስጥ በሚሰጡ አገልግሎቶች ላይ፣

ሀ) የሥራ ተቋራጮች ፣ የእህል ወፍጮ ቤቶች፣ የትራክተሮች እና ኮምባይን ሀርቨስተሮች አገልግሎት ፪ በመቶ (ሁለት ፐርሰንት)፣

ለ) ሌሎች ፲ በመቶ (አሥር ፐርሰንት)

ተርን ኦቨር ታክስ ይከፈላል።

፭· **የተርን ኦቨር ታክስ ስሌት መሠረት**

ታክሱ የሚሰላበት ዋጋ የዕቃው ወይም የአገልግሎቱ ጠቅላላ የሽያጭ ገቢ ነው።

፮· **የተርን ኦቨር ታክስ ሰብስቦ ገቢ የማድረግ ኃላፊነት**

ዕቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን የሚሸጥ ማንኛውም ሰው በሽያጩ ላይ ሊከፈል የሚገባውን ታክስ ከገዥው ሰብስቦ ለታክሱ ባለሥልጣን ገቢ የማድረግ ግዴታ አለበት። ስለሆነም ሻጩ ስለታክሱ የመጀመሪያ ተጠያቂ ይሆናል።

፯· **ከታክስ ነፃ ስለመሆን**

፩· የሚከተሉት በዚህ አዋጅ ከተጣለው የተርን ኦቨር ታክስ ክፍያ ነፃ ናቸው፤

ሀ) ቢያንስ ሁለት ዓመት ያገለገለ መኖሪያ ቤት ሽያጭ እና የመኖሪያ ቤት ኪራይ፣

ለ) የፋይናንስ አገልግሎቶች፣

ሐ) ለማንቲሞች እና ሜዳሊያዎች ጥናት አገልግሎት ከሚውሉት በስተቀር የአገር ውስጥና የውጭ አገር ገንዘቦችን እና የዋስትና ሰነዶችን ማስራጨት፣

መ) በሃይማኖት ድርጅቶች የሚሰጡ የእምነት ወይም ከእምልኮት ጋር የሚገናኙ አገልግሎቶች፣

ሠ) የሕክምና አገልግሎቶች እና አግባብ ባለው የመንግሥት መሥሪያ ቤት በሚወጣ መመሪያ መሠረት በሐኪም የሚታዘዙ መድኃኒቶች፣

ረ) በትምህርት ተቋማት የሚሰጡ የማስተማር አገልግሎቶች እንዲሁም ለሕፃናት ጥበቃ በመዋዕለ ሕፃናት የሚሰጡ አገልግሎቶች፣

ሰ) ለሰብዓዊ ዕርዳታ የሚውሉ ዕቃዎችና አገልግሎቶች፣

ሸ) የኤሌክትሪክ፣ የኬሮሲን እና የውሃ አቅርቦት፣

ቀ) የትራንስፖርት አገልግሎቶች፣

በ) ማንኛውንም የሥራ እንቅስቃሴ ለማከናወን ለሚሰጥ ፈቃድ ለመንግሥት የሚፈጸም ክፍያ፣

ተ) ከ፷ በመቶ በላይ ሠራተኞቹ አካል ጉዳተኞች የሆኑበት አካል ጉዳተኞችን ቀጥሮ የሚያሠራ ድርጅት የሚያቀርባቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶች፣

ቸ) መፃሕፍት።

፪· የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትር በሚያወጣው መመሪያ በሌሎች ዕቃዎችና አገልግሎቶች ላይ የሚከፈለው ታክስ ቀሪ እንዲሆን ሊፈቅድ ይችላል።

3. *Scope*

Unless exempted under Article 7 of this Proclamation or directives to be issued thereunder, Turnover Tax shall be payable on goods supplied and services rendered by persons not registered for Value Added Tax.

## SECTION TWO

### The Rate of Tax and Exemption

4. *Rate of Turnover Tax*

The Turnover Tax shall be:

1) 2% (two percent) on Goods sold locally
2) for Services rendered locally;
   (a) 2% (two percent) on Contractors, grain mills, tractors and combine-harvesters;
   (b) 10% (ten percent) on others.

5. *Base of Computation of the Turnover Tax*

Base of computation of the Turnover Tax shall be the gross receipts in respect of goods supplied or services rendered.

6. *Obligation to Collect and Transfer the Turnover Tax*

A person who sells goods and services has the obligation to collect the Turnover Tax from the buyer and transfer same to the Tax Authority. Hence, the seller is principally accountable for the payment of the tax.

7. *Exemption*

1) The following shall be exempted from Turnover Tax:
   (a) the sale or transfer of a dwelling used for a minimum of two years, or the lease of a dwelling;
   (b) the rendering of financial services;
   (c) the supply of national or foreign currency (except for that used for numismatic purposes) and of securities;
   (d) the rendering by religious organizations of religious or other related services;
   (e) the supply of prescription drugs specified in directives issued by the relevant government agency, and the rendering of medical services;
   (f) the rendering of educational services provided by educational institutions, as well as child care services for children at pre-school institutions;
   (g) the supply of goods and rendering of services in the form of humanitarian aid;
   (h) the supply of electricity, kerosene, and water;
   (i) the provision of transport;
   (j) permits and license fees;
   (k) the supply of goods or services by a workshop employing disabled individuals if more than 60% of the employees are disabled; and
   (l) the supply of books.
2) The Minister of Finance and Economic Development may, by directive, exempt other goods and services.

፫· በዚህ አንቀጽ የተዘረዘሩት ከታክስ ነፃ የመሆን መብቶች አፈፃፀም የገቢዎች ሚኒስትር በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

## ክፍል ሦስት
## የታክሱ አስተዳደር ሥርዓት

፰· ታክሱን የማስተዳደር እና ሪፖርት የማቅረብ ኃላፊነት

፩· በዚህ አዋጅ መሠረት የተርን ኦቨር ታክሱን ስሌት በትክክል የማከናወን፣ የታክሱን ማስታወቂያ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለታክሱ ባለሥልጣን የማቅረብና ታክሱን በጊዜው የመክፈል ኃላፊነት የታክስ ከፋዩ ነው።

፪· የተርን ኦቨር ታክስን የማስተዳደር ኃላፊነት የታክሱ ባለሥልጣን ነው።

፱· የሂሳብ መዝገብ ስለመያዝ

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፮/፲፱፻፺፬ አንቀጽ ፵፰ የሂሳብ መዝገብ የመያዝ ግዴታ የተጣለባቸው ታክስ ከፋዮች ለተርን ኦቨር ታክስ አወሳሰን እንዲያገለግል በገቢ ግብር አዋጁ የታዘዘውን የሂሳብ መዝገብ መያዝ አለባቸው።

፲ የተርን ኦቨር ታክስ ማስታወቂያ ስለማቅረብ እና ታክሱን ስለመክፈል

፩· የተርን ኦቨር ታክስ ከፋዮች፣

ሀ) እያንዳንዱ የሂሳብ ጊዜ በተጠናቀቀ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለታክስ ባለሥልጣን የተርን ኦቨር ታክስ ማስታወቂያ ማቅረብ፣

ለ) የተርን ኦቨር ታክስ ማስታወቂያ ለማቅረቢያ በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ በሂሳብ ጊዜው መከፈል ያለበትን ታክስ የመክፈል፣

ግዴታ አለባቸው።

፪· ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም "የሂሳብ ጊዜ" ማለት፣

ሀ) በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፮/፲፱፻፺፬ የደረጃ 'ሀ' ግብር ከፋዮች ተብለው የሚታወቁ እና ለተጨማሪ እሴት ታክስ የመመዝገብ ግዴታ የሌለባቸው ታክስ ከፋዮች በየወሩ፣

ለ) በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፮/፲፱፻፺፬ በተደነገገው መሠረት የሂሣብ መዝገብ ለሚይዙ የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች በኢትዮጵያ የበጀት ዓመት ወይም በታክሱ ባለሥልጣን ሲፈቀድ በአውሮፓ ዘመን አቆጣጠር ከዓመቱ የመጀመሪያ ቀን ጀምሮ የሚቆጠር የየሦስት ወር ጊዜ፣

ሐ) በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፮/፲፱፻፺፬ በተደነገገው መሠረት የሂሣብ መዝገብ ለማይዙ የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች የበጀት ዓመቱ፣

ነው።

፲፩· የተርን ኦቨር ታክስ አወሳሰን

፩· የታክሱ ባለሥልጣን የታክስ ከፋዩን ሂሣብ ከመረመረ በኋላ ታክስ ከፋዩ ሊከፍል የሚገባውን ታክስ አሳንሶ ያስታወቀ መሆኑን የደረሰበት እንደሆነ ተጨማሪ የታክስ ውሳኔ ይሰጣል።

፪· የታክስ ከፋዩ የሂሣብ መዛግብትና ደጋፊ ሰነዶቹ በማናቸውም ምክንያት በታክስ ባለሥልጣኑ ዘንድ ተቀባይነት ካላገኙ ወይም በታክስ ባለሥልጣኑ እንዲቀርቡ ተጠይቆ ካልቀረቡ ወይም የሂሣብ መዛግብትና ደጋፊ ሰነዶች ከሌሉ የታክሱ ባለሥልጣን ታክሱን ባለው መረጃ ወይም የዕቃውን ወይም የአገልግሎቱን የአገር ውስጥ ገበያ ዋጋ፣ ዋጋው የማይታወቅ ከሆነ የተመሳሳዩን የገበያ ዋጋ መሠረት በማድረግ ይወስናል።

፫· በገቢ ግብር አዋጅ በተደነገገው መሠረት የሂሣብ መዝገብ የማይዙ የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች የተርን ኦቨር ታክስ በቁርጥ ይወሰናል። በቁርጥ የሚከፈለው ተርን ኦቨር ታክስ ስሌት መሠረት ለገቢ ግብር መሠረት የሆነው ጠቅላላ ገቢ ነው።

3) The Minister of Revenue may, by directive, determine the scope and manner of exemptions provided for in this Article.

## SECTION THREE
## Administrative Procedures

8. *Responsibility for Administration and Reporting*

1) The responsibility for the correct calculation and timely payment of Turnover Tax and presentation of a return to the Authority by the prescribed deadline rests on the tax payer in accordance with this Proclamation.

2) The Turnover Tax is administered by the Tax Authority.

9. *Records*

Tax payers subject to the record-keeping requirement of Article 48 of the Income Tax Proclamation No. 286/2002 shall keep the records prescribed therein for use in determining Turnover Tax.

10. *Filing of Turnover Tax Return and Payment*

1) Tax payers subject to Turnover Tax shall:
   (a) file a Turnover Tax return with the Tax Authority within one month after the end of every accounting period;
   (b) pay the tax for every accounting period by the deadline for filing the Turnover Tax return.

2) For purposes of this Article "Accounting period" shall mean:
   (a) for taxpayers classified as category 'A' taxpayers under the Income Tax proclamation No. 286/2002, but are not required to register for VAT, the calendar month;
   (b) for category "B" taxpayers who are required to keep records under the Income Tax Proclamation No. 286/2002 each three month period commencing from the first day of the Ethiopian fiscal year or when approved by the Tax Authority, the first day of the Gregorian calendar year;
   (c) for Category "C" taxpayers, who are not required to keep records under Income Tax Proclamation No. 286/2002, the fiscal year.

11. *Assessment of the Tax*

1) If, after review by the Tax Authority, it appears that a person has understated his tax obligation, the Authority shall issue an additional assessment.

2) If, for any reason, the books of account are unacceptable to the Tax Authority, or if the tax payer fails to submit same when requested by the Tax Authority, or if no books of account and supporting documents are maintained, the Tax Authority shall assess the tax on the basis of information available to it or on the basis of market price of such good or service in the local market or if the market price is unknown, on the basis of the market price of an equivalent good or service.

3) A presumptive turnover tax shall be payable by Category "C" taxpayers who are not required to keep records. The base for the presumptive turnover tax shall be the total turnover used as base for the income tax.

፬· የታክሱ ባለሥልጣን የሰጠው የታክስ ውሣኔ በማስታ ወቂያ ተዘጋጅቶ ለታክስ ከፋዩ ይላካል። የውሣኔ ማስታ ወቂያ የመላኩ አፈፃፀም በገቢ ግብር አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ይፈፀማል።

፭· የታክሱ ባለሥልጣን በንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ተጨማሪ የታክስ ውሳኔ የሰጠ እና የታክስ ውሣኔ ማስታወቂያ የደረሰው ሰው ማስታወቂያው በደረሰው በ፴ ቀን ውስጥ እንዲከፍል የተጠየቀውን ተጨማሪ ታክስ ያልከፈለ ወይም በውሳኔው ላይ ቅሬታ ካለው በአንቀጽ ፳፩ መሠረት ይግባኝ ያላቀረበ እንደሆነ ጥፋተኛ ነው።

፮· በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፰ መሠረት ታክስ ከፋዩ ታክሱን አስታውቆ ከከፈለበት የበጀት ዓመት መጨረሻ አንስቶ በ፭ ዓመት ጊዜ ውስጥ የታክሱ ባለሥልጣን የታክሱን ልክ ወስኖ ቀሪ ሂሣብ መኖሩን ካላስታወቀ የተከፈለው ታክስ በቂና የመጨረሻ ይሆናል። ሆኖም ታክስ ከፋዩ ገቢውን ያላስታወቀ ወይም የተጭበረበረ የገቢ ማስታ ወቂያ ያቀረበ እንደሆነ የታክሱ ባለሥልጣን በማና ቸውም ሌላ ሕግ የተደነገገው ይርጋ ሳያግደው ታክሱን በማናቸውም ጊዜ መወሰን ይችላል።

## ክፍል አራት
## የታክሱ አሰባሰብ አፈፃፀም

**፲፪· የታክሱ ባለሥልጣን ሥልጣን**

በዚህ አዋጅ ሌሎች አንቀጾች ከተጠቀሱት በተጨማሪ የታክሱ ባለሥልጣን የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፤

፩· ይህን አዋጅ በሥራ ላይ የማዋል እና የማስፈፀም ኃላፊነት የታክሱ ባለሥልጣን ይሆናል፤

፪· በማናቸውም ሌላ ሕግ ውስጥ ተቃራኒ የሆኑ ድንጋጌዎች ቢኖሩም፣ የታክሱ ባለሥልጣን በማናቸውም ጊዜ በታክስ ከፋይ የቀረቡ ማንኛቸውንም መግለጫዎች፣ ሰነዶችና የሂሣብ መዝገቦች ለማረጋገጥ፣

ሀ) ሕጋዊ ሥልጣን የተሰጣቸውን ተቆጣጣሪዎች ወደታክስ ከፋዩ የንግድ ወይም የሙያ ሥራ ቦታ በመላክ የሂሣብ መግለጫዎችን፣ ሰነዶችን እና የሂሣብ መዝገቦችን ወይም ገቢና ወጪን የሚያሳዩ ሰነዶችን፣ ለንግድ የተከማቹ ዕቃዎችን ወይም ሌሎች ዕቃዎችን ለማመሳከርና ለመመርመር፣

ለ) ታክስ ከፋዩን ወይም የሂሳብ መዝገቦችን እና ሰነዶችን ወይም መረጃን ለማግኘት የሚችለውን ወይም እነዚህኑ የመጠበቅ ኃላፊነት የተሰጠውን ማንኛውንም የታክስ ከፋዩን ተቀጣሪ በአመቺ የታክሱ ባለሥልጣን የሥራ ሰዓቶች እና በጽ/ቤቱ ተገኝቶ ለሚቀርቡለት ለጉዳዩ አግባብ ያላቸው ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጥና የተባሉትንም ሰነዶች እንዲያቀርብ ለማድረግ፣

ሐ) ማዘጋጃ ቤት፣ የፋይናንስ ተቋም ወይም ማንኛ ውንም የፌዴራል ወይም የክልል መንግሥት መሥሪያ ቤት ጨምሮ ማንኛውም ሰው ስለታክስ ከፋዩ የሚያውቀውን መረጃ ወይም የሥራ እንቅ ስቃሴ ዝርዝር እንዲገልፅ ለማድረግ ይችላል።

**፲፫· ታክስ ለመሰብሰብ ሀብት ስለመያዝ**

፩· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) የተደነገገው እንደተ ጠበቀ ሆኖ ማናቸውም በዚህ አዋጅ የተጣለው ታክስ የሚፈለግበት ሰው በአንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ (፭) ወይም በአንቀጽ ፳፩ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተደነገገው መሠረት ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ የታክሱ ባለሥ ልጣን የዚህን ታክስ ከፋይ ሀብት በመያዝ ለሚፈለግበት ታክስ እና ንብረቱን ለመያዝ የተደረገውን ተጨማሪ ወጪ ለመሸፈን እንዲውል ለማድረግ ሕጋዊ ሥልጣን

4) The assessment made shall be prepared in an assessment notification and be delivered to the tax payer. Delivery of the assessment notification shall be made in accordance with provisions of the Income Tax Proclamation.

5) If the Authority makes an additional assessment under Sub-Article (1), and within 30 days of the notice and demand the person assessed does not pay the additional assessment or appeal the assessment as provided under Article 21, the person is in default.

6) If the Tax Authority fails to assess the tax and notify the taxpayer of the amount still due within five years from the date of declaration and payment of the tax by the taxpayer in accordance with Article 8 of this Proclamation, the tax so paid shall be final and conclusive. In case where the taxpayer has not declared his income or has submitted a fraudulent declaration, no time limit provided in any other law shall bar the assessment of the tax by the Tax Authority.

## SECTION FOUR
## Collection Enforcement

12. *Powers and Duties of the Tax Authority*

In addition to the powers vested in it in other provisions of this Proclamation, the Tax Authority shall have the following powers and duties:

1) The implementation and enforcement of this Proclamation shall be the duty of the Tax Authority.

2) Notwithstanding any provisions to the contrary in any other law, the Tax Authority shall be empowered to investigate any statements, records and books of account submitted by any taxpayer at any time by:

(a) sending duly accredited inspectors to check the statements, records and books of account, or any vouchers, stocks or other material items at the person's place of business or practice;

(b) requiring the person or any employee who has access to or custody of any information, records or books of account to produce the same and to attend during normal office hours at any reasonably convenient tax office and answer any questions relating thereto;

(c) requiring any person including a municipality, body, financial institution, department or agency of Federal or Regional Government to disclose particulars of any information or transactions relating to a certain taxpayer.

13. *Seizure of Property to Collect Tax*

1) Subject to Sub-Article (4) of this Article, if any person liable to pay any tax imposed by this Proclamation is in default under Sub-Article (5) of Article 11 or Sub-Article (2) of Article 21, it shall be lawful for the Authority to collect such tax (and such further amount as shall be suffient to cover the expenses of the seizure) by seizing any property

፪· ለዚህ ክፍል አፈፃፀም "መያዝ" በማናቸውም መንገድ መያዝን፣ እንዲሁም የተርንኦቨር ታክስ የሚፈለግበት ሰው የሆነ ገንዘብ ወይም ንብረት በእጁ ከሚገኝ ሰው ታክስ መሰብሰብን ይጨምራል። በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፮) በተነገረው መሠረት ካልሆነ በስተቀር መያዝ የሚቻለው የመያዙ ትዕዛዝ በተሰጠበት ጊዜ በይዞታ ሥር የሚገኝ ንብረት እና የመያዙ ተግባር በሚከናወንበት ጊዜ ፀንቶ ያለ ግዴታን በተመለከተ ብቻ ነው። የታክሱ ባለሥልጣን የታክስ ከፋዩን ሀብት በሚይዝበት ጊዜ የፖሊስ ሠራዊት አባል እንዲገኝ ሊጠይቅ ይችላል። ባለሥልጣኑ ከዚህ በላይ በተመለከተው መሠረት ሀብቱን ከያዘበት ቀን አንስቶ ከሚቆጠር ከ፲ (አሥር) ቀናት ጊዜ በኋላ በሐራጅ ወይም በባለሥልጣኑ በተፈቀደ በማናቸውም ሌላ ዘዴ የያዘውን ንብረት መሸጥ ይችላል። ሆኖም ንብረቱ የሚበላሽ ከሆነ የንብረቱን ባህርይ ከግምት ውስጥ በማስገባት ተገቢ መስሎ በሚታየው ጊዜ ሊሸጠው ይችላል።

፫· ማናቸውም የተያዘ ንብረት ለመያዙ ምክንያት የሆነውን የታክስ ዕዳ ለመሸፈን በቂ ሳይሆን የቀረ እንደሆነ የታክሱ ባለሥልጣን ከታክስ ከፋዩ ላይ የሚፈለገው የታክስ ዕዳ እና ከዚህ ጋር የተያያዙ ልዩ ልዩ ወጪዎች ተከፍለው እስከሚጠናቀቁ ድረስ የታክስ ዕዳው የሚፈለግበትን ሰው ሌሎች ሀብቶች መያዝ ይችላል።

፬· ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ (፩) በተደነገገው መሠረት ባልተከፈለ የታክስ ዕዳ ምክንያት ንብረት መያዝ የሚቻለው የታክሱ ባለሥልጣን ሀብቱን የመያዝ ሀሳብ እንዳለው አስቀድሞ ለታክስ ከፋዩ በጽሑፍ ካስታወቀው በኋላ ይሆናል። በዚህ ዓይነት የሚሰጠው ማስታወቂያ ሀብቱ ከመያዙ ከ፴ (ሰላሳ) ቀን በፊት ለታክስ ከፋዩ ሊደርሰው ይገባል።

፭· የታክሱ ባለሥልጣን የታክሱን አሰባሰብ የሚያደናቅፍ ሁኔታ መኖሩን የተረዳ እንደሆነና በንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው የ፴ ቀን የጊዜ ገደብ ሳይጠበቅ ታክሱ ወዲያውኑ እንዲከፈል ለማድረግ ጥያቄ ካቀረበ እንዲሁም ታክስ ከፋዩ ለመክፈል ፈቃደኛ ካልሆነ ንብረትን በመያዝ ታክስ የመሰብሰቡ አፈፃፀም ሕጋዊ ይሆናል።

፮· ማናቸውም ንብረት የተያዘ ወይም እንዲያዝ የታሰበ ከሆነ ስለዚሁ ንብረት ማስረጃ የሚሆን ወይም መግለጫ የያዘ ሰነድ ወይም መዝገብ በእጁ የሚገኝ ወይም በቁጥጥሩ ሥር ያለ ማናቸውም ሰው በታክሱ ባለሥልጣን ጥያቄ ሲቀርብለት ሰነዱን ወይም መዝገቡን ለማስረጃነት ማቅረብ አለበት።

፯· በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የተከበረ ወይም በአፈጻጸም ላይ ያለ ወይም በዋስትና የተያዘ ካልሆነ በስተቀር ማናቸውም በታክስ ምክንያት የተያዘ ንብረት በእጁ የሚገኝ ወይም ለታክስ ከፋዩ ማናቸውም ግዴታ ያለበት ሰው የታክሱ ባለሥልጣን ሲጠይቀው የያዘውን ሀብት ለታክሱ ባለሥልጣን የማስረከብ ወይም ያለበትን ግዴታ የመፈጸም ኃላፊነት አለበት።

፰· ማናቸውም ሰው የታክሱ ባለሥልጣን ሲጠይቀው አንድን የተያዘ ንብረት ለማስረከብ ፈቃደኛ ሳይሆን የቀረ እንደሆነ በተያዘው ንብረት መጠን በግል ተጠያቂ ይሆናል። ሆኖም ተጠያቂነቱ ለንብረቱ መያዝ ምክንያት ከሆነው የታክስ ዕዳ መጠን (በታክሱ ዕዳ ላይ የሚታሰበውን ወጪ እና ወለድ ጨምሮ) ሊያልፍ አይችልም።

፱· በንዑስ አንቀጽ (፰) ከተመለከተው የግል ተጠያቂነት በተጨማሪ ንብረቱን የያዘው ሰው ንብረቱን ለማስረከብ ፈቃደኛ ያልሆነው ያለበቂ ምክንያት ከሆነ በንዑስ አንቀጽ (፰) መሠረት የሚፈለገውን የገንዘብ መጠን ፶ ፐርሰንት (ሃምሳ በመቶ) በተጨማሪ እንዲከፍል ይደረጋል።

2) For purposes of this Section, the term "seizure" includes seizure by any means, as well as collection from a person who owes money or property to the person liable for Turnover Tax. Except as provided in Sub-Article (3) and (6), a seizure shall extend only to property possessed by and obligations owed to the taxpayer existing at the time the seizure is made. The Authority may request the attendance of a police officer during the seizure. Where the Authority seizes any property as provided herein above, it shall have the right to sell the seized goods at public auction or in any other manner approved by the Authority not less than 10 days after the seizure, except that when the goods seized are perishable, the Authority can sell the goods after any reasonable period having regard to the nature of the goods.

3) Whenever any property on which seizure had been made is not sufficient to satisfy the claim for which seizure is made, the Authority may, there after and as may be necessary, proceed to seize other property liable to seizure of the person against whom the claim exists until the amount due from such person, together with all expenses, is fully paid.

4) Seizure under Sub-Article (1) on property of any person in default with respect to any unpaid tax may be made only after the Authority has notified such person in writing of the intention to make such seizure. The notice shall be delivered not less than thirty 30 (thirty) days before the day of the seizure.

5) If the Authority makes a finding that the collection of the tax is in jeopardy and demanded for immediate payment of such tax (without regard to the 30 days period) provided in Sub-Article (1) and )4) upon failure or refusal of the taxpayer to pay such tax, collection of the tax by seizure of property before such period shall be lawful.

6) If a seizure has been made or is about to be made on any property, any person having custody or control of any books or records containing evidence or statements relating to the property subject to seizure shall, on demand, exhibit such books or records to the Authority.

7) Any person in possession of (or obligated with respect to) property subject to seizure shall, on demand, surrender such property to the Authority (or discharge such obligation), except such part of the property is, at the time of such demand, subject to a prior secured claim of creditors and subject to an attachment or execution under any judicial process.

8) Any person who fails or refuses to surrender any property subject to seizure, when demanded by the Authority, shall be personally liable to the government in a sum equal to the value of the property not so surrendered, but not exceeding the amount of tax for the collection of which seizure has been sought (together with costs and interest on such sum).

9) In addition to the personal liablity imposed by Sub-Article (8), if the failure or refusal to surrender is without reasonable cause, such person shall be liable for an additional charge equal to fifty per cent (50%) of the amount recoverable under Sub-Article (8).

፲· በዚህ አንቀጽ መሠረት በይዞታው ሥር ያለውን ንብረት ያስረከበ ወይም በታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን ገንዘብ ከታክሱ ባለሥልጣን በተጠየቀው መሠረት ገቢ ያደረገ ማናቸውም ሰው ካስረከበው ንብረት ወይም ገቢ ካደረገው ገንዘብ ጋር በተያያዘ የታክስ ግዴታውን ባልተወጣው ታክስ ከፋይ ወይም ማናቸውም ሌላ ሰው ከሚፈለግበት ዕዳ ወይም ካለበት ግዴታ ነፃ ይሆናል።

፲፬· <u>በሀብት ላይ የሚቀርብ የቀደምትነት መብት ጥያቄ</u>

፩· ዋስትና የተሰጣቸው የሌሎች አበዳሪዎች የቅድሚያ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በዚህ አዋጅ መሠረት ታክስ ተከፋይ ከሚሆንበት ቀን አንስቶ ተከፍሎ እስከአለቀበት ጊዜ ድረስ ታክስ የመክፈል ግዴታ ባለበት ሰው ሀብት ላይ የታክሱ ባለሥልጣን የቀደምትነት መብት ይኖረዋል።

፪· ማናቸውም ሰው ታክስ የመክፈል ግዴታውን ባለመወጣት ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ የታክሱ ባለሥልጣን በጥፋት ምክንያት ያልተከፈለውን ታክስ እና ታክሱን ለማስከፈል የሚደረገው እንቅስቃሴ የሚያስከትለውን ወጪ ማስከፈል እንዲቻል የታክሱ ዕዳ የሚፈለግበት ሰው ሀብት በዋስትና ተይዞ እንዲቆይ ንብረቱን ለመዘገበው አካል የፅሑፍ ትዕዛዝ የሚሰጥ መሆኑን የሚገልጽ ማስጠንቀቂያ ለተመዘገበው ሰው ይሰጣል።

፫· በንዑስ አንቀጽ (፪) የተገለፀው ማስጠንቀቂያ የደረሰው ታክስ ከፋይ ማስጠንቀቂያው በደረሰው በ፴ ቀን ውስጥ ታክሱን ያልከፈለ እንደሆነ የታክሱ ባለሥልጣን ለንብረት መዝጋቢው ባለሥልጣን የተመዘገበው ሰው ሀብት ባልተከፈለው የታክስ ዕዳ መጠን በዋስትና ተይዞ እንዲቆይ ትዕዛዝ ይሰጣል።

፬· በንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የታክሱ ባለሥልጣን ታክስ የሚፈለግበት ሰው ሃብት በዋስትና ተይዞ እንዲቆይ ትዕዛዝ የሰጠ ሲሆን፣ መዝጋቢው ባለሥልጣን ማናቸውንም ክፍያ ሳይጠይቅ ንብረቱ በዋስትና እንዲያዝ የደረሰውን ትዕዛዝ እንደማናቸውም በሀብቱ ላይ እንዳለ የመያዣ ሰነድ ይመዘግባል። ቀደም ሲል የተሰጠ የመያዣ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የዋስትናው ምዝገባ የሚፈለገውን ታክስ ለማስከፈል በማናቸውም መልኩ በሕግ እንደተሰጠ መያዣ ወይም እንደማናቸውም ሌላ ዕዳ ወይም ክፍያ ሆኖ ይቆጠራል።

፲፭· <u>ታክስ ከፋዩ ስላለው ጥበቃ</u>

በዚህ ክፍል ፬ መሠረት የተያዘ ማናቸውም ንብረት የሚያዘው፣ የሚጠበቀው ፣ እና የሚመዘገበው በታክሱ ባለሥልጣን ብቻ ይሆናል። ማናቸውም ሌላ የመንግሥት አካል በዚህ ክፍል መሠረት የተያዘውን ንብረት ማናቸውንም ሌላ ምክንያት መሠረት በማድረግ እንዲሰጠው ወይም እንዲተላለፍለት መጠየቅ አይችልም። የተያዘ ንብረት የተሸጠ እንደሆነ ከሽያጩ ከተገኘው ገንዘብ ውስጥ ታክስ ከፋዩ ከሚፈለግበት ዕዳ በላይ የሆነው ገንዘብ ለንብረቱ ባለቤት ወዲያውኑ ይመለሳል።

፲፮· <u>የተረካቢ ግዴታ</u>

፩ በዚህ አንቀጽ ውስጥ "ተረካቢ" ማለት በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኝን የታክስ ከፋዩን ሀብት በተመለከተ፣

ሀ) የኩባንያ የንብረት አጣሪ ሆኖ የተሰየመ፣

ለ) ከፍርድ ቤት ውጪ ወይም በፍርድ ቤት የተሾመ ተረካቢ፣

ሐ) በኪሣራ ውስጥ የሚገኝ ድርጅት ባለአደራ፣

መ) መያዣ በይዞታው ሥር የሚገኝ፣

ሠ) የሞተን ሰው ንብረት የሚያስተዳድር፣ ወይም

10) Any person in possession of the property of a taxpayer in default and who surrenders such property or pays the tax in occordance with this Article to which the owner is liable, shall be discharged from any obligation or liability to the deliquent or to any other person arising from such surrender or payment.

14. *Preferential Claim to Assets*

1) Subject to the prior secured claims of creditors, the Authority has a preferential claim upon the assets of the person liable to pay the tax until the tax is paid from the date on which tax becomes due and payable under this Proclamation.

2) Where a person is in default of paying tax, the Authority may, by notice in writing, inform that person of the Authroity's intention to apply to the Registering Authority to register a security interest in any asset which is owned by that person, to cover any unpaid tax together with any expense incurred in recovery proceedings.

3) If the person on whom a notice has been served under Sub Article (2) fails to pay the amount specified in the notice within 30 days after the date of service, the Authority may, by notice in writing, direct the Registering Authority that the asset, to the extent of the defaulter's interest therein, shall be the subject of security for the total amount of unpaid tax.

4) Where the Authority has served a notice on the Registering Authority under Sub–Article (3), the Registering Authority shall, without fee, register the notice of security as if the notice were an instrument of mortgage over or charge on, as the case may be, such asset, and such registration shall, subject to any prior mortgage or charge, operate while it subsists in all respects as a legal mortgage over or charge on the asset to secure the amount due.

15. *Taxpayer's Safeguards*

Any property seized under this Section 4 shall be seized, held, and accounted for only by the Authority. No other agency of the government may require the property seized to be transferred or given over to it for any cause whatsoever. If any property seized is sold, any portion of the proceeds in excess of the person's liabilities shall be returned promptly to the owner.

16. *Duties of Receivers*

1) In this Article "receiver" means a person who, with respect to an asset in Ethiopia of a registered person, is:

(a) a liquidator of a company;

(b) a receiver appointed out of court or by a court;

(c) a trustee for an unrehabilitated insolvent;

(d) a mortgagee in possession;

(e) an executor of a deceased's estate; or

ረ) በሕግ ችሎታ የሌለውን ሰው የንግድ ሥራ የሚያ ካሂድ፣

ማናቸውም ሰው ነው።

፪· በኢትዮጵያ ውስጥ ያለ ንብረት ተረካቢ ሆኖ የተሾመ ወይም ንብረት በይዞታው ሥር የተደረገ ተረካቢ ከተሾመበት ወይም ንብረቱ በይዞታው ሥር ከተደረገበት ከሁለቱ ከቀደመው ቀን ጀምሮ በ፲፬ ቀን ጊዜ ውስጥ የተሾመ ወይም በይዞታው ሥር ያለ መሆኑን ለታክሱ ባለሥልጣን ማስታወቅ አለበት።

፫· የታክሱ ባለሥልጣን ንብረቱ በተረካቢው ይዞታ ሥር ያለ ሰው የሚፈለግበትን የታክስ ዕዳ ለመሸፈን የሚያስፈልገውን የገንዘብ መጠን ለተረካቢው በጽሑፍ ያስታውቃል።

፬· ተረካቢው፣

ሀ) በንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት በታክስ ባለሥልጣኑ የተገለፀውን የገንዘብ መጠን ወይም ከማስታወቂያው በኋላ በስምምነት የተደረሰበትን ሌላ የገንዘብ መጠን ከንብረቱ ሽያጭ ላይ ቀንሶ ለብቻው ያስቀምጣል።

ለ) ተቀንሶ ለብቻው በተቀመጠው የገንዘብ መጠን ልክ የተረከበው ንብረት ባለቤት ከሆነው ሰው ለሚፈለገው የታክስ ዕዳ ተጠያቂ ይሆናል።

ሐ) በዚህ አንቀጽ የተመለከተው ቢኖርም ከታክስ ቀደምትነት ያለውን ማናቸውንም ዕዳ ሊከፍል ይችላል።

፭· ተረካቢው በንዑስ አንቀጽ (፫) የተጠቀሰውን ታክስ በተመለከተ በንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት ተቀንሶ ለብቻው እንዲቀመጥ የተደረገውን የገንዘብ መጠን በዚህ አንቀጽ ለተጠቀሰው ታክስ ካላዋለ ተቀንሶ ለብቻ በተቀመጠው ገንዘብ ልክ በግል ተጠያቂ ይሆናል።

፲፯· ለውጦችን ስለማስታወቅ

ማናቸውም ታክስ ከፋይ፣

፩· ስሙ ፣ አድራሻው ፣ የንግድ ሥራው ቦታ ፣ አደረጃጀቱ፣ ወይም ታክስ የሚከፈልበትን ዋንኛው የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ወይም የሚያከናውናቸውን ተግባራት ዓይነት፣

፪· ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ሥራ እንቅስቃሴ የሚከናወንበትን አድራሻ ወይም ስም ፣

የቀየረ እንደሆነ ይህንኑ ለታክሱ ባለሥልጣን በ፳፩ ቀናት ጊዜ ውስጥ ማስታወቅ አለበት ።

## ክፍል አምስት
## ይግባኝ የሚቀርብበት ሥርዓት

፲፰· የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ

የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ አባላት በታክስ ባለሥልጣኑ ኃላፊ አቅራቢነት እንደአግባብነቱ በገቢዎች ሚኒስትር ወይም አግባብ ባለው የክልል ባለሥልጣን ይሰየማሉ ።

፲፱· የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴው ስለሚኖረው ሥልጣንና ተግባር

፩· ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለታክሱ ባለሥልጣን ሆኖ ፣

ሀ) በታክስ ከፋዮች መቀጫ እንዲነሳ ፣ ወለድ ቀሪ እንዲደረግ ወይም የታክስ ግዴታ እንዲሻሻል የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን ለመመርመርና ውሳኔ ለመስጠት ፣

ለ) ከቀረቡት አቤቱታዎች ጋር ግንኙነት ያላቸውን ማናቸውንም የጽሑፍ ማስረጃዎች ወይም መረጃዎች መሰብሰብ ፤

ሐ) በምርመራ ላይ የሚገኘውን ጉዳይ በሚመለከት ረገድ ቀርቦ የሚጠየቀውን ጥያቄ እንዲመልስ ከታክሱ አወሳሰን ጋር በቀጥታ ወይም ቀጥታ ባልሆነ መንገድ ግንኙነት ያለውን ማንኛውንም ሰው የመጥራት ፣

(f) any other person conducting a business on behalf of a person legally incapacitated.

2) A receiver shall notify, in writing, his appointment or his possession to the Authority within 14 days after having been appointed to the position or taken possession of an asset in Ethiopia, whichever first occurs.

3) The Authority may, notify a receiverin writing of the amount which appears to the Authroity to be sufficient to provide for tax which is or will become payable by the person whose assets are in the possession of the receiver.

4) A receiver:
   (a) shall set aside, out of the proceeds of sale of an asset, the amount specified by the Authority under Sub–Article (3), or such a lesser amount as is subsequently agreed on by the Authority;
   (b) is liable to the extent of the amount set aside for the tax of the person who owned the asset; and
   (c) may notwithstanding any provision of this Article pay any debt that has priority over the tax referred to in this Article.

5) A receiver is personally liable to the extent of any amount required to be set aside under Sub-Article (4) for the tax referred to in Sub-Article (3) if, the receiver fails to comply with the requirements of this Article.

17. *Notification of Changes*

A registered taxpayer shall notify the Authority, in writing, of
   (a) any change in the name, address, place of business, constitution, or nature of the principal taxable activity or activities of the person; and
   (b) any change of address from which, or name in which, a taxable activity is carried on by the registered person,

within 21 days following such change.

## SECTION FIVE
## *Appeal Procedure*

18. *Review Committee*

Members of the Review Committee shall be appointed by the Minsiter of Revenue or the competent authority of the regional government, as appropriate, upon the recommendation of the head of the Authority.

19. *Powers and Duties of the Review Committee*

1) The Review Committee shall be accountable to the head of the Authority and shall have the following duties:
   (a) to examine and decide on all appolications submitted by tax payers for compromise of penality, interest and on the tax assessed;
   (b) to gather any written evidence or information relevant to the matter submitted to it;
   (c) to summon any person who directly or indirectly has dealt with the assessment, to appear before it to answer questions about the case under its investigation; and

መ) የታክሱ ባለሥልጣን የሰጠው የታክስ ውሣኔ ትክክለኛ ፣ የተሟላ እና ይህንን አዋጅ ጠብቆ የተሰጠ መሆኑን የማረጋገጥ ፣

ሥልጣን ይኖረዋል ።

፪· የአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ከታክስ ከፋዮች የሚቀርበውን አቤቱታ ሊያይ የሚችለው ታክስ ከፋዩ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ በደረሰው በ፲ ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ካቀረበ ነው ።

፫· የታክሱ ባለሥልጣን ኃላፊ የኮሚቴውን የውሳኔ ሀሳብ ሊያጸድቀው ወይም በውሳኔ ሀሳቡ ካልተስማማ ምክን ያቱን በመግለጽ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ለኮሚቴው ሊመልሰው ይችላል።

፳· <u>መቀጫን ስለማንሳት</u>

ኮሚቴው እንደአግባብነቱ የገቢዎች ሚኒስትር ወይም አግባብ ያለው የክልል ባለሥልጣን በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በታክስ ከፋዩ ላይ የተጣለው አስተዳደራዊ መቀጫ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲነሳ ማድረግ ይችላል ።

፳፩· <u>ይግባኝ</u>

፩· በታክሱ ባለሥልጣን የተላለፈውን የተጨማሪ ታክስ ውሳኔ የሚቃወም ማናቸውም ታክስ ከፋይ የታክስ ውሳኔ ማስታወቂያ ከደረሰው ወይም በአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በ፴ (ሠላሳ) ቀናት ውስጥ በባለሥልጣኑ የተወሰነውን ተጨማሪ ታክስ ፶ በመቶ (ሃምሳ ፐርሰንት) ባለሥልጣኑ ዘንድ በማስያዝ ለይግባኝ ሰሚ ጉባዔ ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የይግባኝ አቤቱታ ቀርቦ የግብር ይግባኝ ጉባዔ ታክስ ከፋዩ በተጨማሪ የተወሰነበትን ታክስ በሙሉ ወይም በከፊል የመክፈል ግዴታ እንዳለበት ውሳኔ ከሰጠበት ቀን አንስቶ በ፴ ሠላሣ ቀን ጊዜ ውስጥ ታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን ተጨማሪ ታክስ ካልከፈለ ጥፋተኛ ነው ።

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ይግባኝ ካልቀረበ በባለሥልጣኑ የተወሰነው ተጨማሪ ታክስ ትክክለኛና የመጨረሻ ሆኖ ወዲያውኑ ተከፋይ ይሆናል ።

፬· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በገቢ ግብር አዋጅ ስለይግባኝ የተደነገጉ አንቀፆች እንደአግባብነታቸው በዚህ አዋጅ መሠረት የተወሰኑ ታክሶችን በሚመለከት ለሚቀርቡ ይግባኞች ተፈፃሚ ይሆናሉ ።

፳፪· <u>የማስረዳት ኃላፊነት</u>

የተወሰነው ግብር በዝቷል ወይም የታክሱ ባለሥልጣን የሰጠው ውሳኔ ትክክል አይደለም በሚል በሚቀርብ ክርክር የማስረዳቱ ኃላፊነት የተወሰነውን ታክስ ወይም የባለሥል ጣኑን ውሳኔ የሚቃወመው ሰው ይሆናል ።

## <u>ክፍል ስድስት</u>
## <u>አስተዳደራዊ ቅጣቶች</u>

፳፫· <u>የታክስ ማስታወቂያን በጊዜ ባለማቅረብ ስለሚፈፀም ቅጣት</u>

፩· በዚህ አዋጅ በሌላ አኳኋን እንዲፈጸም ከተወሰነው በስተቀር ፣ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ የታክስ ማስታወቅ ግዴታውን ያልተወጣ ታክስ ከፋይ ለዘገየበት ለእያን ዳንዱ ወር ወይም የወሩ ከፊል ለሆነው ጊዜ ፣ ያልተከፈ ለውን ታክስ ፭ በመቶ (አምስት ፐርሰንት) ፳፭ በመቶ (ሃያ አምስት ፐርሰንት) እስኪሞላ ድረስ መቀጫ ይከፍላል ።

፪· የታክስ ማስታወቂያ መቅረብ ባለበት ወር ወይም የወሩ ክፍል በሆነው ጊዜ የታክስ ማስታወቂያ ያላቀረበ ሰው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ መሠረት የሚከፍለው መቀጫ ከብር ፶ ሺ (ሃምሳ ሺህ) አይበልጥም ።

፫· ለዚህ አንቀጽ አፈፃፀም ያልተከፈለ ታክስ ነው የሚባለው በታክስ ማስታወቂያ ላይ መታየት በነበረበት እና ታክሱ መከፈል ባለበት ቀን በተከፈለው ታክስ መካከል ያለው ልዩነት ነው ።

(d) to review the accuracy, completeness, and compliance with this Proclamation of the tax assesment made by the Authority.

2) The Committee shall only review applications submitted to it within 10 days of receipt of tax assessment notification.

3) The Head of the Tax Authority may approve the recommendations or remand the case, with his observations, to the Committee for further review.

20. *Waiver of Penalty*

The Review Committee may waive administrative penalties, wholly or partly, in accordance the directives to be issued by the Minister of Revenue or by the competent authority of the regional government, as may be appropriate.

21. *Appeal*

1) Any person who objects to an additional assessment made by the Authority has the right to appeal, within 30 days from the receipt of assessment notification, or from the date of decision of the Review Committee, to the Tax Appeal Commission by depositing in cash with the Authority 50% (fifty percent) of the additional tax assessed.

2) If a person appeals in accordance with Sub-Article (1) and the Tax Appeal Commission determines that the person is liable for the additional assessment, he shall be in default unless he pays the additional assessment determined by the Tax Appeal Commission within thirty (30) days of the rendition of such a decision.

3) If no appeal is made within the period prescribed in Sub-Article (1) of this Article, the Additional assessment of the tax made by the Authority shall be deemed to be correct and final, and shall be immediately payable.

4) Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, the provisions of the Income Tax Proclamation relating to appeals shall, mutatis mutandis, apply to appeals regarding taxes imposed by this Proclamation.

22. *Burden of Proof*

The burden of proving that an assessment is excessive or that a decision of the Authority is wrong is on the person objecting to the assessment or decision.

## SECTION SIX
## *Administrative Penalties*

23. *Penalties for Late Filing*

1) Except as otherwise provided in this Proclamation, a person who faiis to file a timely return is liable for a penalty equal to 5 per cent of the amount of tax underpayment for each month (or portion thereof) during which the failure continues, upto 25% (twenty five per cent) of such amount.

2) The penalty under Sub-Article (1) of this Article is limited to 50,000 Birr for the first month (or portion thereof) in which no return is filed.

3) For purposes of this Article, an underpayment of tax is the difference between the tax required to be shown on the return and the amount of tax paid by the due date.

፬· በማናቸውም ሁኔታ የሚጣለው ቅጣት ቀጥሎ ከተመለከቱት ከዝቅተኛው ያነሰ አይሆንም ፤
ሀ) ብር ፲ ሺህ (አሥር ሺህ ብር)፣
ለ) በታክስ ማስታወቂያ ላይ መመልከት ከነበረበት የታክስ መጠን ፻ በመቶ (አንድ መቶ ፐርሰንት)።

፳፬· ዘግይቶ በተከፈለ ታክስ ላይ ስለሚታሰብ ወለድ
ሀ) መከፈል በነበረበት ጊዜ ላልተከፈለ ታክስ፣ መከፈል ከነበረበት ቀን እስከተከፈለበት ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ ታክስ ከፋዩ ወለድ የመክፈል ግዴታ አለበት።
ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (ሀ) መሠረት የሚከፈለው ወለድ የማስከፈያ ልክ ባለፈው የሩብ ዓመት በንግድ ባንኮች ሥራ ላይ በዋለው ከፍተኛው የማበደሪያ ወለድ ምጣኔ ላይ ፳፭ በመቶ (ሃያ አምስት ፐርሰንት) ታክሎበት ይሆናል ።

## ክፍል ሰባት
## የወንጀል ቅጣቶች

፳፭· በታክስ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች ስለሚመሩበት ሥነ ሥርዓት
በዚህ ክፍል የተዘረዘሩት በታክስ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉን በመተላለፍ የሚፈፀሙ በመሆኑ ክሱ የሚመሠረተው ፣ የሚታየው እና ይግባኝ የሚቀርበው በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት መሠረት ይሆናል ።

፳፮· ሕግን በመጣስ ታክስ ስላለመክፈል
የሰበሰበውን ታክስ ያላስታወቀ ወይም የሚፈለግበትን ታክስ ያልከፈለ ማናቸውም ሰው ወንጀል እንደፈፀመ ይቆጠራል ። ስለሆነም በዚህ አዋጅ ክፍል ፮ መሠረት ከሚጣልበት መቀጫ በተጨማሪ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከ፭ ዓመት በማያንስ እሥራት ይቀጣል ።

፳፯· የሐሰት ወይም አሳሳች መረጃ ስለማቅረብ
፩· ማናቸውም ታክስ ከፋይ
ሀ) ለታክሱ ባለሥልጣን ሠራተኛ አንድን ነጥብ በተመለከተ የሀሰት ወይም አሳሳች መረጃ ያቀረበ ፣ ወይም
ለ) ለታክሱ ባለሥልጣን ሠራተኛ ሊቀርብ ከሚገባው መግለጫ ውስጥ መግለጫውን አሳሳች ሊያደርግ በሚችል አኳኋን መካተት የሚገባቸውን ነጥቦች ያስቀረ እንደሆነ፣
የወንጀል ክስ ይመሠረትበታል።
፪· የሐሰት መግለጫው የተሰጠው ወይም መካተት የሚገባው ነጥብ የተተወው ያለበቂ ምክንያት የሆነ እንደሆነ፣
ሀ) የመግለጫው ትክክለኛ ያለመሆን ሊደረስበት ያለመቻሉ ሊከፈል የሚገባው ታክስ ከብር ፩ ሺህ በማይበልጥ አንሶ እንዲከፈል የሚያደርግ ከሆነ ታክስ ከፋዩ ከብር ፲ ሺህ በማያንስ እና ከብር ፳ ሺህ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና ከአንድ ዓመት በማያንስ እና ከሦስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል።
ለ) አንሶ እንዲከፈል የሚደረገው ታክስ ከብር ፩ ሺህ የሚበልጥ ከሆነ ከብር ፳ ሺህ በማያንስ እና ከብር ፩፻ሺህ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና ከሦስት ዓመት በማያንስ እና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል።
፫· የሐሰት መግለጫ የተሰጠው ወይም መካተት የሚገባው ነጥብ እንዲካተት ያልተደረገው ሆን ተብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት የሆነ እንደሆነ፣
ሀ) የመግለጫው ትክክለኛ ያለመሆን ሊደረስበት ያለመቻሉ ሊከፈል የሚገባው ታክስ ከብር ፩ ሺ በማይበልጥ አንሶ እንዲከፈል የሚያደርግ ከሆነ ታክስ ከፋዩ ከብር ፶ ሺ በማያንስ እና ከብር ፩፻ ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ እና ከአምስት ዓመት በማያንስ እና ከአሥር ዓመት በማይበልጥ እሥራት፣

4) In any event the penalty may not be less than the smaller of the two amounts:
(a) 10,000 birr (ten thousand Birr);
(b) 100 percent of the amount of tax required to be shown on the return.

24. *Late Payment Interest*
(a) If any amount of tax is not paid by the due date, the person liable is obliged to pay interest on such amount for the period from the due date to the date the tax is paid.
(b) The interest rate under Sub-Article (a) of this Article is set at 25% (twenty five percent) over and above the highest commercial banks, lending interest rate that prevailed during the preceding quarter.

## SECTION SEVEN
## *Criminal Offences*

25. *Procedure in Tax Offence Cases*
A tax offence under this Section is a violation of the criminal law of Ethiopia and shall be charged, prosecuted, and appealed in accordance with the Ethiopian Criminal Procedure Code.

26. *Tax Evasion*
A person who evades the declaration or payment of tax, commits an offence and, in addition to any penalty under Section 6, may be prosecuted and, on conviction, be subject to imprisonment for a term of not less than 5 (five) years.

27. *Making False or Misleading Statements*
1) A taxpayer who,
(a) makes a false or misleading in a material particularstatement to a tax officer of the Authority, or
(b) omits, from a statement made to an officer of the Authority, any matter or thing without which the statement is misleading in a material particular.

commits an offence and is liable on conviction.

2) Where the false statement or omission is made without reasonable excuse,
(a) and if the inaccuracy of the statement undetected would have resulted in an underpayment of tax by an amount not exceeding 1,000 Birr, the taxpayer shall be subject to a fine of not less than 10,000 Birr and not more than 20,000 Birr and imprisonment for a term of not less than one (1) year and not more than three (3) years: and
(b) if the underpayment of the tax is in an amount exceeding 1,000 Birr, to a fine of not less than 20,000 birr and not more than 100,000 Birr, and to imprisonment for a term of not less than three (3) years and not more than five (5) years,

3) Where the false statement or omission is made knowingly or recklessly,
(a) and if the inaccuracy of the statement were undetected would have resulted in an underpayment of tax by an amount not exceeding 1,000 Birr, the taxpayer shall be subject to a fine of not less than 50,000 Birr and not more than 100,000 Birr and to imprisonment for a term of not less than five (5) years and not more than ten (10) years; and

ለ) አንሶ እንዲከፈል የሚደረገው ታክስ ከብር ፩ ሺ የሚበልጥ ከሆነ ከብር ፸፭ ሺ በማያንስ እና ከብር ፪፻ ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ እና ከ፲ ዓመት በማያንስ እና ከ፲፭ ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል።

፳፰· የታክሱን ባለሥልጣን ሥራ ስለማሰናከል

፩· ማንኛውም ሰው፤

ሀ) በዚህ አዋጅ መሠረት ሥራውን በማከናወን ላይ ያለን የታክስ ባለሥልጣን ሠራተኛ ተግባር ያሰናከለ ወይም ለማሰናከል የሞከረ፣ ወይም

ለ) የአዋጁን አፈፃፀም በማናቸውም ሌላ አኳኋን ያሰናከለ ወይም ለማሰናከል የሞከረ እንደሆነ፣ ወንጀል መፈፀሙ ተረጋግጦ ሲፈረድበት ከብር ፩ ሺ በማያንስ እና ከብር ፩፻ ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ እና በሁለት ዓመት እሥራት ይቀጣል።

፪· ለንዑስ አንቀጽ (፩) አፈፃፀም የሚከተሉት እና እነዚህን የመሳሰሉ ሌሎች ተግባሮች የታክሱን ባለሥልጣን ሥራ የማሰናከል ተግባራት ሆነው ይወሰዳሉ፤

ሀ) የታክስ ከፋዩን ገቢ አስገኚ የሥራ እንቅስቃሴዎች የሚመለከቱ ሰነዶችን፣ ሪፖርቶችን ወይም ሌሎች ማናቸውንም መረጃዎች ለመመርመር የታክሱ ባለ ሥልጣን ሲጠይቅ ፈቃደኛ ሆኖ ያለመገኘት፣

ለ) የታክሱ ባለሥልጣን ለጥያቄ እንዲቀርብ ሲያዝ ፈቃደኛ ሆኖ ያለመገኘት፤

ሐ) የታክሱ ባለሥልጣን ሠራተኛ ወደታክስ ከፋዩ የንግድ ሥራ ቦታ ለመግባት ያለውን መብት መገደብ።

፳፱· ለውጥን ያለማስታወቅ

አንቀጽ ፲፯ በሚያዘው መሠረት በሁኔታዎች ላይ የተደረጉ ለውጦችን ለታክሱ ባለሥልጣን ያላስታወቀ ማናቸውም ሰው ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ፣

ሀ) ጥፋቱ የተፈፀመው ሆን ተብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት የሆነ እንደሆነ ከብር ፲ ሺ በማያንስ የገንዘብ መቀጮ እና በአንድ ዓመት እሥራት፣

ለ) በሌሎች ሁኔታዎች ከብር ፭ ሺ በማያንስ የገንዘብ መቀጮ እና በ፮ ወር እሥራት፣

ይቀጣል።

፴· በታክሱ ባለሥልጣን ሠራተኞች የሚፈፀሙ ጥፋቶች

፩· የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ለማስፈጸም በታክስ ባለሥልጣኑ የተቀጠረ ሠራተኛ ወይም የቀድሞ ተቀጣሪ የነበረ፣

ሀ) በሕግ መሠረት ሊያገኘው ከሚገባ ክፍያ ወይም ሽልማት ውጪ ከተቀጠረበት ተግባር ጋር በተያያዘ ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የገንዘብ ወይም ሌላ ዓይነት ክፍያ ወይም ስጦታ እንዲደረ ግለት የጠየቀ ወይም የተቀበለ፣ ለክፍያው ወይም ለስጦታው ተስፋ ወይም መያዣ የጠየቀ ወይም የተቀበለ፣ ወይም

(b) if the underpayment of the tax is in an amount exceeding 1,000 Birr, the tax payer shall be subject to a fine of not less than 75,000 Birr and not more than 200,000 Birr, and to imprisonment for a term of not less than ten (10) years and not more than fifteen (15) years.

28. *Obstruction of Tax Administration*

1) Any person who:
   (a) obstructs or attempts to obstruct an officer of the Authority in the performance of duties under this Proclamation, or
   (b) otherwise impedes or attempts to impede the implementation of the Proclamation,

   commits an offence and is liable, on conviction, to a fine of not less than 1,000 Birr and not more than 100,000 Birr, and to imprisonment for a term of two (2) years,

2) For the purposes of Sub-Article (1), the following and other similar actions are considered to constitute obstruction:
   (a) refusal to satisfy the request of the Authority for inspection of documents, reports, or other information relating to a taxpayer's income producing activities;
   (b) non compliance with the Authority's request to report for an interview;
   (c) interference with a tax officer's right to enter the taxpayer's business premises.

29. *Failure to Notify*

A person who fails to notify the Authority of a change as required by Article 17 commits an offence, and on conviction:

(a) where the failure was made knowingly or recklessly, is liable to a fine of not less than 10,000 Birr and to imprisonment for one year; or

(b) in any other cases, to a fine of not less than 5,000 Birr and to imprisonment for a term of six months.

30. *Offences by Tax Officer*

1) Any tax officer or former taxation officer employed in carrying out the provisions of this Proclamation who:
   (a) directly or indirectly asks for, or receives in connection with any of the taxation officer's duties, a payment or reward, whether pecuniary or otherwise, or promise or security for that payment or reward, not being a payment or reward which the officer is lawfully entitled to receive, or

ለ) ከታክስ በሚገኘው ገቢ ላይ ማጭበርበር ወይም ከዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ጋር ወይም ከተሰጠው ኃላፊነት መልካም አፈፃፀም ጋር የሚቃረን ተግባር ለመፈፀም፣ ማድረግ የሚገባውን ከማድረግ ለመታቀብ፣ ተገቢ ያልሆነን ነገር ለመፍቀድ፣ በታክስ ላይ የሚፈፀምን የማጭበርበር ተግባር ለመደበቅ፣ ወይም በሚስጥር ለመተግበር ውል የገባ ወይም በሚገባው ማናቸውም ውል ውስጥ በዚህ ተግባር መተባበሩን የሚያሳይ ስምምነት የሰጠ፣

ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር ፶ ሺ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ እና ከ፲ ዓመት በማያንስ ከ፳ ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል።

፪· የታክስ ባለሥልጣኑ ሠራተኛ የሆነ ወይም የነበረ እና የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ለማስፈጸም የተቀጠረ፣ በኢትዮጵያ ንግድ ሕግ በንግድ ጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣ ከታዘዘው ዓይነት መረጃ በስተቀር፣

ሀ) ታክስን በማስፈጸም ረገድ ባለው ሥልጣን ወይም ግዴታ ምክንያት ያወቀውን የሌላ ሰው ማናቸውንም መረጃ ለማናቸውም ሌላ ሰው ወይም የዚያ ሰው ወኪል ለሆነ ሰው አሳልፎ የሰጠ፣

ለ) በዚህ አዋጅ መሠረት ታክስን በማስፈጸም ረገድ ያለውን ሥልጣን ለመጠቀም ወይም የሥራ ግዴታውን ለመወጣት እንዲያስችል በታክስ ባለሥልጣኑ ዘንድ የሚገኘውን ማናቸውንም መረጃ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ካልሆነ በስተቀር ለሦስተኛ ወገን አሳልፎ የሰጠ እንደሆነ፣

ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር ፲ሺ በማያንስ የገንዘብ መቀጮ እና ከሁለት ዓመት በማያንስ እና ከአምስት ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል።

፫· የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ የታክስ ባለሥልጣኑ ሠራተኛ፣

ሀ) ማናቸውንም ሰነድ ወይም መረጃ፣

(i) ለዚህ አዋጅ ወይም ለማናቸውም ገንዘብ ነክ አዋጅ አፈፃፀም አስፈላጊ በሆነ ጊዜ፣

(ii) በሕግ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት አስፈላጊ ሲሆን፣ ለዋናው ኦዲተር፣

(iii) መረጃ ለመለዋወጥ፣ ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት ኢትዮጵያ ከሌሎች አገሮች ጋር ባደረገችው ስምምነት መሠረት አግባብ ላላቸው የሌሎች አገሮች ባለሥልጣኖች፣

(iv) በሕግ የተሰጠውን ተግባርና ኃላፊነት ለመወጣት አስፈላጊ ሲሆን፣ ለሥነ ምግባርና ለፀረ ሙስና ኮሚሽን፣

(v) ከዚህ በላይ ላልተገለፀ ለማናቸውም ሕግ አስፈጻሚ መ/ቤት ግዴታውን ለመፈፀም የሚያስችለው መረጃ እንዲሰጠው ከገቢዎች ሚኒስቴር በጽሑፍ ሲታዘዝ።

ለ) ኃላፊነታቸውን ለመወጣት አስፈላጊ እስከሆነ ድረስ አንድን ሰው ለይተው የማይጠቅሱ መረጃዎችን ለማናቸውም በመንግሥት ገቢ ሥራ ላይ ለሚያገለግል እና ለስታትስቲክስ መ/ቤት ሠራተኛ፣

ከመስጠት አያግደውም።

፴፩· ሳይፈቀድ ታክስ ስለመሰብሰብ

ማናቸውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት ሳይፈቀድለት ታክስ ወይም እንደታክስ የሚታይ ሌላ ክፍያ የሰበሰበ ወይም ለመሰብሰብ የሞከረ ወንጀል የፈፀመ ሆኖ፣ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ከብር ፶ሺ የማያንስ የገንዘብ መቀጮ እና ከአምስት ዓመት በማያንስ ከአስር ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል።

(b) enters into or acquiesces in an agreement to do or to abstain from doing, permit, conceal, or connive at any act or thing whereby the tax revenue is or may be defrauded or which is contrary to the provisions of this Proclamation or to the proper execution of the taxation officer's duty;

commits an offence and is liable on conviction to a fine of not more than 50,000 Birr and to imprisonment for a term of not less than ten (10) years and not more than twenty (20) years.

2) A tax officer or a former tax officer engaged in carrying out the provisions of this Proclamation, except such information is required by the Commercial Code of Ethiopia to be published in the Trade Gazette, who,

(a) discloses to any person or his representative, any matter in respect of another person, that may, in the exercise of the taxation officer's powers or the performance of the taxation officer's duties under the said provisions, come to the taxation officer's knowledge; or

(b) permits any other person to have access to records in the possession or custody of the Authority, except in the exercise of the taxation officer's powers or the performance of the other's duties under this Proclamation or by order of a court;

commits an offence and is liable on conviction to a fine of not less than 10,000 Birr and to imprisonment for a term of not less than two (2) years and not more than five (5) years.

3) Nothing in this Article shall prevent a taxation officer from disclosing:

(a) any document or information to:

(i) any person where the disclosure is necessary for the purposes of this Proclamation or any other fiscal law;

(ii) the Auditor-General where the disclosure is necessary for the performance of duties entrusted to it by law;

(iii) the competent authority of the government of another country with which Ethiopia has entered into an agreement for the avoidance of double taxation or for the exchange of information, to the extent permitted under the agreement;

(iv) the Ethics and Anti-Corruption Commission where the disclosure is necessary for the performance of duties entrusted to it by law;

(v) a law enforcement agency not described above, where the Minister of Revenue issues written authorization to make disclosures necessary for the enforcement of the laws under the agency's authority; or

(b) to any person in the service of the State in a revenue or statistical department, information which does not identify a specific person where such disclosure is necessary for the performance of the person's official duties.

31. *Unauthorized Tax Collection*

Any person not authorized to collect tax under this Proclamation who collects or attempts to collect tax (or an amount the person describes as tax) commits an offence and is liable on conviction to a fine of not less than 50,000 Birr and to imprisonment for a term of not less than five (5) years and not more than ten (10) years.

፴፪. <u>መርዳት ወይም ማበረታታት</u>

ማናቸውም ሰው የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንዲጣሱ የረዳ፣ ያበረታታ፣ ያነሳሳ፣ ወይም በሚስጥር የተባበረ እንደሆነ እንደዋንኛው ጥፋተኛ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በመጣስ ጥፋት ይፈጽማል። ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን የፈጸመ ሰው፤ ጥፋተኛ መሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ዕርዳታውን ወይም ትብብሩን ለሰጠበት ጥፋት ከተወሰነው የገንዘብ እና የእሥራት ቅጣት ባልበለጠ በገንዘብ እና በእሥራት ይቀጣል።

፴፫. <u>በድርጅቶች የሚፈጸም ጥፋት</u>

፩. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ አንድ ድርጅት ይህንን አዋጅ በመተላለፍ ጥፋት የፈጸመ እንደሆነ ጥፋቱ በተፈጸመ ጊዜ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ የሆነ ማናቸውም ሰው በድርጅቱ የተፈጸመውን ጥፋት እንደፈጸመ ተቆጥሮ በዚህ አዋጅ የተጣለው ቅጣት ተፈጻሚ ይሆንበታል።

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ማናቸውም ድርጅት በዚህ አዋጅ መሠረት ሊከፈል የሚገባውን ወይም አዋጁ እንደታክስ የሚቆጥረውን ማናቸውንም ሌላ ክፍያ ገቢ ሳያደርግ የቀረ እንደሆነ ጥፋቱ ከተፈጸመበት ጊዜ አስቀድሞ በነበሩት ስድስት ወራት ውስጥ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ የነበሩ ሰዎች ከድርጅቱ እና ከሌላው ሰው ጋር በአንድነትና በተናጠል የታክሱ ባለሥልጣን ለሚፈልገው ታክስ እና ሌሎች ክፍያዎች ተጠያቂ ይሆናሉ።

፫. በንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተደነገጉት፤

ሀ) ጥፋቱ የተፈጸመው ግለሰቡ ሳያውቅ ወይም ሳይስማማበት ከሆነ፤

ለ) አንድ ነገሮችን በጥንቃቄ የሚያይ ሰው በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ የጥፋቱን መፈጸም ለመከላከል ይወስዳቸዋል ተብሎ የሚገመቱ ጥንቃቄዎችን፤ ተገቢውን ትጋት እና የአሠራር ጥበብ የተሞላበት እርምጃ ግለሰቡ ወስዶ የተገኘ እንደሆነ፤

ተፈጻሚ አይሆኑበትም።

፬. ለንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) አፈጻጸም "ሥራ አስኪያጅ" ማለት፤

ሀ) የሽርክና ማኅበርን በሚመለከት የሽርክናው ማኅበር አባል ወይም የማኅበሩ ሥራ አስኪያጅ ወይም ከሁለቱ ኃላፊነቶች በአንዱ እንደሚሠራ ሆኖ የሚታይ፤

ለ) ኩባንያን በሚመለከት የኩባንያው የሥራ መሪ፤ ሥራ አስኪያጅ ወይም ማናቸውም ሌላ ሹም ወይም ከእነዚህ ኃላፊነቶች በአንዱ እንደሚሠራ ሆኖ የሚታይ፤

ሐ) የሰዎችን ኅብረት በሚመለከት የኅብረቱ ሥራ አስኪያጅ ወይም በዚሁ ኃላፊነት እንደሚሠራ ሆኖ የሚታይ፤

ነው።

፴፬. <u>በተረካቢዎች የሚፈጸም ጥፋት</u>

፩. ማናቸውም ሰው በአንቀጽ ፲፮ ንዑስ አንቀጽ (፬) በተደነገገው መሠረት ሳይፈጽም የቀረ እንደሆነ፤ ጥፋተኛነቱ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ብር ፭ሺ የገንዘብ መቀጮ እና በአንድ ዓመት እሥራት ይቀጣል።

፪. ማናቸውም ሰው በአንቀጽ ፲፮ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት ለታክስ ክፍያ የሚውለውን ገንዘብ ለይቶ ባለማስቀመጡ ምክንያት በንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ፤ ፍርድ ቤቱ ከገንዘብና እሥራት መቀጮው በተጨማሪ ለይቶ ያላስቀመጠውን የገንዘብ መጠን ለታክሱ ባለሥልጣን ገቢ እንዲያደርግ ሊያዝ ይችላል።

32. *Aiding or Abetting*

A person who aids, abets, incites, or conspires with another person, to commit a violation of this Proclamation, also commits an offence. He may be subject to prosecution and, on conviction, be liable to a fine and imprisonment, not in excess of the amount of fine or period of imprisonment provided for the offence aided or abetted.

33. *Offences by Entities*

1) Subject to Sub-Article (3) of this Article, where an enitity commits an offence, the person who is a manager of that entity at the time the offence is committed, is treated as also having committed the same offence and is liable to a fine and imprisonment under this Proclamation.

2) Subject to Sub-Article (3) of this Article, where an entity commits an offence by failing to pay an amount of tax, including an amount treated by this Proclamation as though it were tax, the person who was a manager of that entity at the time of such failure or was a manager within six (6) months prior to the date of commission is jointly and severally liable with that entity and that other person for the amount due to the Authority.

3) Sub-Articles (1)and(2) do not apply where,

    (a) the offence is committed without that person's knowledge or consent; and

    (b) that person has exercised the degree of care, diligence and skill that a reasonable prudent person would have exercised in comparable circumstances to prevent the commission of the offence.

4) In Sub-Articles (1) and (2), "manager" means,

    (a) in the case of a partnership a partner or manager of the partnership or a person purporting to act in either of those capacities;

    (b) in the case of a company, a director, manager, or officer of the company or a person purporting to act in any of those capacities;

    (c) in the case of an association of persons, a manager or a person purporting to act in that capacity.

34. *Offences by Receivers*

1) A person who fails to comply with the requirements of Article 16(4) commits an offence and is liable, on conviction to a fine of 5,000 Birr and to imprisonment for a term of one (1) year.

2) Where a person is convicted of an offence under Sub Article (1) of this Article for failing to set aside an amount as required under Article 16(4), the court may, in addition to imposing a fine and prison sentence, order the convicted person to pay, to the Authority, an amount not exceeding the amount which the person failed to set aside.

፴፭· የጥፋተኞችን ስም በጋዜጣ አትሞ ስለማውጣት

፩· የታክሱ ባለሥልጣን በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ ፳፭–፴፬ የተደነገጉትን የወንጀል ጥፋቶች በመፈጸም የተፈረደ ባቸው ሰዎች ስም ዝርዝር በየጊዜው በዕለታዊ ጋዜጦች ታትሞ እንዲወጣ ያደርጋል።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ታትሞ የሚወጣው ዝርዝር፤

ሀ) የድርጅቱን ወይም የግለሰቡን ስም እና አድራሻ፤

ለ) ባለሥልጣኑ ተገቢ ነው ብሎ የሚያምንበትን የወን ጀሉን አፈጻጸም ዝርዝር፤

ሐ) ጥፋቱ የተፈጸመበትን የግብር ዘመን ወይም ዘመናት፤

መ) ሳይከፈል የቀረውን ግብር መጠን፤

ሠ) በተጨማሪ እንዲከፍል የተወሰነበት ግብር ካለ ይህንኑ፤

የሚገልፅ ይሆናል

## ክፍል ስምንት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፴፮· የመተባበር ግዴታ

፩· ይህን አዋጅ በሥራ ላይ ለማዋል የፌዴራል እና የክልል መንግሥታት ባለሥልጣኖችና ወኪሎቻቸው በተጨ ማሪም ድርጅቶች፣ የቀበሌ መስተዳድሮች እና ማኅበራት ሁሉ ከታክሱ ባለሥልጣን ጋር የመተባበር ግዴታ አለባቸው።

፪· ሀ) በይግባኝ ቀጠሮ ላይ ካልሆነ ወይም የታክሱ ባለሥ ልጣን የተራዘመ የታክስ መክፈያ ጊዜ ካልሰጠ በስተቀር፣ ታክስ ከፋዩ የሚፈለግበትን ግብር በወቅቱ የከፈለ ስለመሆኑ ወይም አዲስ ታክስ ከፋይን በሚመለከት የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር ካላቀረበ በስተቀር ፣ ፈቃድ ሰጪ ሚኒስቴር ፣ ማዘጋጃ ቤት፣ የፌዴራል ወይም የክልል መሥሪያ ቤት አዲስ የንግድ ሥራ ፈቃድ መስጠት ወይም ማደስ አይችልም።

ለ) የታክሱ ባለሥልጣን ታክስ ከፋዩ ያለበትን ግዴታ ስለመፈጸሙ የምስክር ወረቀት የማይሰጥ ሲሆን ስለዚሁ ያለውን ምክንያት በመዘርዝር ለጠያቂው ይሰጣል።

ሐ) የምስክር ወረቀት አልሰጥም በማለቱ ወይም የንግድ ሥራ ፈቃድ በመሠረዙ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን በሰጣቸው ምክንያቶች ቅር የተሰኘ ማንኛውም ታክስ ከፋይ ቅሬታውን ለአቤቱታ አጣሪ ኮሚቴ ሊያቀርብ ይችላል።

፴፯· የሚኒስትሩ ሥልጣን

በዚህ አዋጅ ሌሎች አንቀፆች ከተገለፀው በተጨማሪ ሚኒስትሩ ለኢኮኖሚ ፣ ለማኅበራዊ ወይም ለአስተዳደር ምክንያቶች ወይም በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር ፪፻፹፮/፲፱፻፺፬ አንቀጽ ፵፪(ለ) በተዘረዘሩት ምክንያቶች በዚህ አዋጅ ከተጣለው ታክስ ክፍያ በሙሉ ወይም በከፊል ነፃ የማድረግ ሥልጣን ተሰጥቶታል ።

፴፰· መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

የገቢዎች ሚኒስትር ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የሚረዱ መመሪያ ዎችን ለማውጣት ይችላል።

፴፱· ስለመሻር

ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ የሽያጭና ኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር ፷፰/፲፱፻፹፭ (እንደተሻሻለ) ተሰርዟል።

35. *Publication of Names*

1) The Authority shall from time to time publish by notice in a Gazette a list of persons who have been convicted of offences under any of the provisions of Articles 25 to 34 of this proclamation.

2) The list published in terms of Sub-Article (1) shall specify:

(a) the name, address, and principal enterprise of the person;

(b) such particulars of the offence as the Authority may think fit;

(c) the tax period or tax periods in which the offence occurred;

(d) the amount or estimated amount of the tax evaded; and

(e) the amount, if any, or the additional tax imposed.

## SECTION EIGHT
## Miscellaneous Provisions

36. *Duty to Cooperate*

1) All Federal and Regional government authorities and their agencies, Bodies, Kebele Administrations and Associations shall have the duty to cooperate with the Tax Authority in the enforcement of this Proclamation.

2) (a) No Ministry, Municipality, Department or Office of the Federal or Regional Government shall issue or renew any license to any taxpayer unless the applicant produces a certificate from the Tax Authority to the effect that tax due in respect of the preceding year or years have been paid, or where the taxpayer is seeking license for the first time a taxpayer identification number (TIN) issued by the Tax Authority, unless an appeal is pending, or time for payment is extended by the Tax Authority.

(b) If the Tax Authority refuses to issue a certificate it shall, on demand by the applicant for the license, provide him or it with a written statement of its reasons therefor.

(c) Any applicant who is aggrieved by the reasons stated by the Tax Authority for refusing to issue a certificate or by the revocation of his or its license may appeal in writing to the Review Committee.

37. *Power of the Minister*

The Minister may waive, in whole or in part, the tax levied under this Proclamation for economic, social or administrative reasons or for reasons specified under Article 42(b) of the Income Tax Proclamation No. 286/2002.

38. *Power to Issue Directives*

The Minister of Revenue may issue directives for the proper implementation of this Proclamation.

39. *Repeal*

The Sales and Excise Tax Proclamation No. 68/1993 (as amended) shall be rescinded as from the day on which this Proclamation becomes of full force and effect.

፵· <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት ሳይከፈል የቀረ የሽያጭ ታክስ በሽያጭና ኤክሣይዝ ታክስ አዋጅ በተደነገገው መሠረት የሚሰበሰብ ይሆናል።

፵፩· <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከታህሣሥ ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ታህሣሥ ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ.ም

ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

40. *Transitory Provisions*

All sales tax due prior to the coming into force of this Proclamation shall be collected in accordance with the Sales and Excise Tax Proclamation.

41. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 31st day of December, 2002.

Done at Addis Ababa, this 31st day of December, 2002.

GIRMA WOLDE GIORGIS
PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA